አዲስ አበባ ሚዲያ ምክር ቤት
ADDIS ABABA MEDIA COUNCIL
Email:
office@addisababamediacouncil.com
Website:
www.addisababamediacouncil.com

# የአዲስ አበባ ሚዲያ ምክር ቤት አስቸኳይ መግለጫ
# ግንቦት 26፣ 2018 ዓ.ም

**Nu 2/6/2018/008**

## የኢትዮጵያ እና የአዲስ አበባ ህዝብ፣ እንዲሁም የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አስቀድሞ የተወሰነውን የምርጫ ተብዬ የሽፍጥ ውጤት እንዲቃወሙ እንጠይቃለን!!!

ግንቦት 24፣ 2018 ዓ.ም የአዲስ አበባ ሕዝብ እና መላው የኢትዮጲያ ሕዝብ  በታሪኩ አይቶት የማያውቀውን እጅግ የወረደ የ"ምርጫ" ድራማ ለመታዘብ የበቃበት እለት ሆናል።  አገዛዙ ያዘጋጀው ይህ ሰባተኛ "ምርጫ" ተብዬ፣  በትግራይ 100%፣ በአማራ ቢያንስ 80%፣ በኦሮሚያ በበርካታ አካባቢዎች፣ በአጠቃላይ በኢትዮጲያ ደረጃ እስከ 45 % በሚጠጋ አካቢዎች በአሰጊ ሁኔታ ወይም ምንም ምርጫ ሊደረግ በማይችልበት ሁኔታ የተተወነ ድራማ ነው።

አገዛዙ በምርጫው ድራማ ላይ ሕዝባችንን በግድ እና በኃይል እንዲሳተፍ ለማስገደድ በእጅጉ የባዘነ ቢሆንም፣ ከ18 እስከ 30 የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለው የአዲስ አበባ ብዙሃን ህዝብ እና የአማራ ክልል ህዝብ ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚቻል ደረጃ ያልተሳተፈበት ሁኔታ መከሰቱን፣ በኦሮሚያ ክልል እና በሌሎች የሀገራችን አካባቢዎች ያለው ህዝብም በአብዛኛው በጣም የተቀዛቀዘ ስሜት እንደነበረው መላው ዓለም የታዘበው ሐቅ ነበር።

በተለይ በአማራ ክልል ትኩስ አስከሬን የተሸከሙ ሐዘንተኞችን እና ለመውለድ የተቃረበች ነፍሰ ጡርን በጉልበት አስገድዶ በድራማው ላይ እንዲተውኑ ያደረገ ቢሆንም፣ በአማራ ፋኖ ድንቅ የጀግንነት ተጋድሎ አገዛዙ ያቀዳቸውን ድራማዎች በሚፈለገው ደረጃ እንዳይካሄድ ከሞላ ጎደል ማገድ ተችሏል።

የአዲስ አበባ ሚዲያ ምክር ቤት የተመሰረተው ኦህዴድ/ብልጽግና መራሹን አምባገነናዊ የፋሺስት አገዛዝ ታግሎ ለማታገል እና የአዲስ አበባ ሕዝብ ድምጽ ሆኖ እውነታን ለማጋለጥ እንደመሆኑ መጠን፣ የአገዛዙን ድራማ አውቆ እርቃኑን ላጋላጠው መላው የሀገራችን ህዝብ ታላቅ ምስጋና ያቀርባል።

**የአዲስ አበባ ሕዝብ ሆይ !!!**

ሰኞ፣ ግንቦት 24 2018 የተካሄደው ሰባተኛ "ምርጫ" ድራማ ዓለም አቀፍ የምርጫ ሂደቶችን መስፈርት ሟሟላት ሳይችል ቀርቶ የከሸፈ ቢሆንም፣ አገዛዙ ነፃ ምርጫ የተደረገ ለማስመሰል አስቀድሞ በወጠነው ሴራ፣ በአዲስ አበባ በሚገኙ 15 % ከመቶ የምርጫ ወረዳዎች እጩ ባለማቅረብ "ተቃዋሚዎች ምርጫ አሸነፉ" ብሎ የሀሰት ፕሮፖጋንዳ የሚሰራበትን ሁኔታ አመቻችቷል። በዚህ የምርጫ ድራማ ተቃዋሚዎች ተወዳድረው ያሸነፉት የምክር ቤት ወንበር እንደሌለ እና ከአገዛዙ በስጦታ የተቀበሉት መሆኑን ለአፍታም መዘንጋት የለብህም። በዚህ ምርጫ ድምፅህ አልተሰማም፣ በውጤቱም አልተወከልክም።

ህዝባችን ሆይ --- አገዛዙ በአዲስ አበባ በተለየ ሁኔታ ባሰፈነው አፓርታዳዊ ሥርዓት ላለፉት ስምንት ዓመታት የፈጸመብህን አስቃቂ ወንጀል ለተጨማሪ አምስት ዓመታት ለማስቀጠል ዓይኑን በጨው አጥቦ መጥቶብሃል። ይህ የምርጫ ድራማ ለህልውና ትግልህ ቆርጠህ መነሳት እንዳለብህ ጥሩ ማሳያ ነው። በህልውና ትግልህ የአዲስ አበባ ምክር ቤት አብሪ ኮከብ ሆኖ ከጎንህ ይቆማል።



Addis Ababa Media Council
Promoting Responsible Media & Public Trust
addisababamediacouncil3@gmail.com
facebook.com/share/1DyFF43NAp
tiktok.com/@addis.ababa.media?_r1&_t=ZP-961itK4BoM
hleps:// x.com/aamediacouncil?s=21

**የኢትዮጲያ ሕዝብ ሆይ !!!**

መቀመጫቸውን በመዲናችን አዲስ አበባ ካደረገው የአህጉራችን የአፍሪካ ሕብረት እና ኢጋድ በስተቀር፣ አብዛኞቹ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች በዚህ ምርጫ አንገኝም እንዲሉ ካደረጓቸው ምክንያቶች መካከል:-

1ኛ. የኢትዮጲያ ምርጫ ቦርድ ነፃነቱን የሚያረጋግጡ ተሀድሶአዊ የማሻሻያ ለውጦች ያላደረገ ተቋም በመሆኑ፣
2ኛ. ከገዢው የብልጽግና ፓርቲ ነጻ የሆኑ እና ጠንካራ ተቃዋሚዎች የማይሳተፉበት ምርጫ በመሆኑ፣
3ኛ. በጦርነት እና በጦርነት ስጋት በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ እና መሰል ክልሎች ያለው ሕዝብ በምርጫው የማይሳተፉ በመሆናቸው የሚሉት ይገኙባቸዋል።

ይህም ሆኖ ግን፣ አገዛዙ የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማሳሳት ሴራ ከመወጠን አልገታውም። በዚህም መሠረት፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ በ48 የፌድራል ፓርላማ የምርጫ ወረዳዎች እጩዎችን ባለማቅረብ፣ "ተቃዋሚዎች በርካታ ወንበሮችን አሸነፉ" የሚል የድህረ - ምርጫ ፕሮፓጋንዳ ለመስራት ተዘጋጅቶ ይገኛል። የኢትዮጲያ ህዝብ በዚህ የሐሰት ፕሮፓጋንዳ እንዳትዘናጋ። ስጦታ የተቀበለ ተቃዋሚ እንጂ ተወዳድሮ ያሸነፈ የለም። በዚህ ምርጫ የኢትዮጲያ ህዝብ ድምፅ አልተሰማም፣ አልተወከለምም። መጪው የፌድራል ፓርላማ የአንተ አይደለም ፤ የብልፅግና ነው።

**የኢትዮጵያ እና የአዲስ አበባ ህዝብ፣ እንዲሁም የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አስቀድሞ የተወሰነውን የ"ምርጫ 2018" ተብዬ የሽፍጥ ውጤት እንዲቃወሙ እንጠይቃለን!!!**

**ስንተባበር እንጠነክራለን፣ እናሸንፋለን !!!**

**የአዲስ አበባ ሚዲያ ምክር ቤት፣**
**ግንቦት 26፣ 2018 ዓ ም።**



Addis Ababa Media Council
Promoting Responsible Media & Public Trust
addisababamediacouncil3@gmail.com
facebook.com/share/1DyFF43NAp
tiktok.com/@addis.ababa.media?_r1&_t=ZP-961itK4BoM
hleps:// x.com/aamediacouncil?s=21